# በ ዝክረ ቅዱሳት አንስት ዘተዋሕዶ - ፩

# የትርጉም ሥራ ላይ የተደረገ የመጽሐፍ ዳሰሳ

ገብረአብ ሓጎስ[1]

## ፩. መግቢያ

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከገዳማትና ገዳማዊ ሕይወት ጋር የተያያዘ ነው። ገዳማት ከሚሰጡት መንፈሳዊና ማኅበረ- ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ጎን ለጎን የቤተ ክርስቲያንንና የሀገርን ታሪክ በመሰነድ ረገድ የራሳቸውን በጎ አስተዋጽኦ አድርገዋል፤ እያደረጉም ነው። ነገር ግን ይህ መረጃን ሰንዶ ለትውልድ የማስቀመጥና የማስተላለፍ ሂደት በሚፈለገው ስፋትና ጥራት ተከናውኖአል ለማለት አይቻልም። አብዛኛው ትኩረት የአበው ቅዱሳንን ሕይወት ወደመመዝገቡ ያደላ ነው። መጻሕፍቱን በአምስት ክፍል ያዘጋጀው የአቡ ሰይፈን[2] የሴቶች አንድነት ገዳምም[3] ሆነ የውርስ ትርጉም ባለቤቷ አዜብ በርሄ እንደሚሉት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት አንስት ተጋድሎ የቅዱሳን አበውን ያክል በስፋት ተነግሯል፤ ተጽፏል ወይም ታውቋል ለማለት እንደማይቻል ይጠቁማሉ። የቅዱሳት አንስትን ድንግልናዊ ሕይወት፣ እንዲሁም ገዳማዊና ምንኵስናዊ ተመክሮ ለቀጣዩ የቤተ ክርስቲያናችን ትውልድ ማስተዋወቁ ፋይዳው ከፍ ያለ ነው። ለዚህም ነው ይህንን ጽሑፍ ለማዘጋጀት የተነሣሣሁት።

በየአቡ ሰይፈን የሴቶች አንድነት ገዳም ተዘጋጅቶ በአዜብ በርሄ የተተረጎመው ይህ መጽሐፍ (**ዝክረ ቅዱሳት አንስት ዘተዋሕዶ ፩**) በግብፅም ሆነ በሌላው ዓለም የነበሩ ቅዱሳት አንስት ደናግል ሕይወትን፣ ቤተ ክርስቲያን ለትውልድ እንድትደርስ ያደረጉትን ተጋድሎ፣ ደናግል ቅዱሳት አንስት የኖሩበትን ቦታ፥ የአኗኗር ሁኔታቸውን፣ ደናግል ቅዱሳት አንስት ገዳማትን በማስፋፋትና ሥርዓተ ገዳም ከመጠበቅ አንጻር የነበራቸውን አስተዋጽኦ እንድናውቅ ከማድረጉም በላይ፣ ብዙ ትኩረት ያልተሰጠው የደናግል ቅዱሳት አንስት ታሪክ ብዙዎች ትኩረት ሰጥተው እንዲያጠኑ ለማነሣሣት የጎላ ሚና ይኖረዋል። እንደ ሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም የቅዱሳት አንስት የሕይወት ታሪክ እምብዛም ያልተጻፈ፣

ያልተነገረና የማይታወቅ በመሆኑ የዚህ መጽሐፍ ዳሰሳ[4] ማቅረብ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት አንስት ተጋድሎ ለማጥናትም ሆነ ለተተኪ ትውልድ ለማስተላለፍ መንገድ ጠቋሚ በመሆኑ አስፈላጊ ያደርገዋል።[5]

የግብፅ ገዳማት በግብፅ ቤተ ክርስቲያንና በመላው ዓለም ያላቸው አሻራ ከፍተኛ ነው። በመዳከም ላይ የነበሩትን የግብፅ ገዳማት ዳግም እንዲያብቡና ለብዙ አብያተ ክርስቲያናት በምሳሌነት እንዲጠቀሱ የጣማፍ ኄራኒ ድርሻ ከፍ ያለ ነው። ይህ መጽሐፍ በቅድስት ኄራኒ ሕይወትና ቅድስቲቱ ለግብፅ ገዳማት ዳግም ማበብ ያበረከተችውን አስተዋጽኦ በሰፊው የሚዳስስ ነው። እኔም በብዙ እየተፈተኑ ላሉ ገዳሞቻችን አንዳች መፍትሔ እንድንፈልግ የሚያግዝ ሆኖ ስላገኘሁት የመጽሐፉን ዳሰሳ ለአንባብያን ለማጋራት ሞክሬያለሁ። በሌሎች ሀገራት አብያተ ክርስቲያናት እንደሚታየው ሁሉ በእኛም ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት አንስት ደናግልና መነኮሳይያት የሕይወት ተሞክሮ (የአበው ቅዱሳንን ያክል ያልተነገረና ያልተጻፈ በመሆኑ) መዘከሩ ጠቃሚ ነው የሚል እምነት አለኝ። የዚህ መጽሐፍ ተርጓሚ ከዚህ ቀደም በነገረ ቅዱሳን ዙርያ ባበረከተቻቸው መጻሕፍት ከፍተኛ ልምድ ያካበተች በመሆኗ፣ መጽሐፉ በቅዱሳት አንስት ዙርያ ሰፊ ግንዛቤ ሊሰጥ እንደሚችል በመገመት ለዳሰሳ መርጬዋለሁ።

## ፪. አጠቃላይ ዳሰሳ

*ዝክረ ቅዱሳት አንስት ዘተዋሕዶ - ፩* በ፭ ክፍልና በ፳፫ ምዕራፎች የተደራጀ ሲሆን፣ በአጠቃላይ ፩፻፵ ገጾች ያሉት መጽሐፍ ነው። የመጀመሪያ ኅትመቱ ነሐሴ ፳፻፲፫ ዓ.ም ሲሆን ጃጃው አታሚዎች እና ዴቨሎፐርስ ኃ. የተ/የግ/ማ አሳትሞታል። የመጽሐፉ ዋና ዓላማ ሲገልጽም "ስለ ገዳማውያንና በረኻውያን አባቶች በተነገረባቸው ጊዜያት ሁሉ ብዙም ትኩረት ስላልተሰጣቸው ወይም በዝምታ ስለታለፉት አንስት ደናግል ሕይወት" መዘከር ነው (አዜብ፣ ፳፻፲፫፣ ገጽ ፳፮)። ይህም የገዳማውያንና የበረኻውያን ደናግል ታሪክ "ግንጥል ጌጥ" እንዳይሆን የጎደለውን ለመሙላት የተነሣ መሆኑን

[4] የዚህ መጽሐፍ ዳሰሳ በማኅበረ ቅዱሳን ቴሌቪዥን "ዓውደ መጻሕፍት" በሚለው ዐምድ ቀርቦ የነበረ ቢሆንም በስፋትና ቅርጽ ባለው መልክ ለማቅረብ እንዲሁም ተደራሽነቱን ለማስፋት ሲባል በዚህ የምርምር መጽሔት እንዲታተም ሆኗል።

[5] የዚህ መጽሐፍ *(ዝክረ ቅዱሳት አንስት ዘተዋሕዶ - ፩)* ተርጓሚ አዜብ በርሄ ከዚህ ቀደም ከሰባት ያላነሱ መጻሕፍትን አድርሳናለች። ከዚህ ቀደም ለኅትመት የበቁ ሥራዎቿ በብዛት በቅዱሳን ሕይወት ላይ ያተኮሩ ናቸው። በተለይም ዝክረ ቅዱሳን ዘተዋሕዶ ፩ - ፬፣ የሰማዕቱ ቅዱስ ሚናስ (ማር ሚና) ገድልና የፓትርያሪክ ቄርሎስ ፮ኛ የሕይወት ታሪክ ለዚህ መጽሐፍ ዝግጅት መሳካት ትልቅ ግብአት እንደሆኗት መገመት ይቻላል። ይህ መጽሐፍ በዚህ ደረጃ ለአንባብያን እንዲደርስ የቀደሙ ሥራዎቿ የሰጧት ልምድና መረዳት መጽሐፉን ተወዳጅና የሚጠበቅ ያደርገዋል።

*ያሳያል። የመጽሐፉ የመጀመሪያው ክፍል ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፣ እንዲሁም በተለያዩ ዘመናት በግብር እርሷን ስለ መሰሏት ደናግል ቅዱሳት አንስት አጠቃላይ ማብራሪያ የሚሰጥ ነው። ክፍሉ በ፲ ምዕራፎች ተከፍሎ የቀረበ ነው። በዚህ ክፍል ከቀረቡት ነጥቦች አንዱ አምላካዊ ስጦታ ለወንድም ሆነ ለሴት ያለ ጾታዊ ልዩነት የሚሰጥ መሆኑና ሴቶች እንደ ወንዶች ሁሉ በገዳማዊ ሕይወት የመሪነት ሚና እንዳላቸው የሚያሳይ ነው። በመቀጠልም ስለ ደናግል አንስት የቀደምት አበውን አስተምህሮ፣ ምክርና አስተያየት ይዳስሳል። ለዚህም ከ ፲ በላይ የሆኑ ቀደምት አበው ስለ ደናግል አንስት የሰጧቸውን አስተምህሮዎች፣ ምክሮችና አስተያየቶች ይተነትናል። ከነዚህም ቅዱስ ጎርጎርዮስ "... የሴት ልጅ የእርሷነቷና የከበረ ማንነቷ መገለጫ፣ ከላይ በገጽታዋ የሚታየው ሥጋዊ አካልዋ ሳይሆን ከውስጥ ያለው በዓይነ ርግብ የተሸፈነው ጥንካሬዋ መሆኑን ተመልከት" በማለት የሴቶችን ውስጣዊ ጥንካሬ ያነሳል (ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ ፴፩)። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በበኩሉ "... ከተጋድሎ ጋር በተያያዘ ሕይወት ውስጥ፣ የሴትነታቸው ልስላሴና ይሉኝተኝነት በምንም መንገድ እንቅፋት አይሆንባቸውም። ምክንያቱም መንፈሳዊ ሕይወት የሚወጠነው በሥጋዊ ሕግ ሳይሆን በሕሊና ፈቃድና ውሳኔ በመሆኑ ነው" በማለት መንፈሳዊ ሕይወት ከውስጣዊ ጽናት እንጂ በአፍአዊ ቅርጽና ጥንካሬ እንዳልሆነ አስረግጦ የመከረውን ይጠቅሳል (ገጽ ፴፯)።*

*ሌላው ጉዳይ ስለደናግል ማኅበር የተገለጸው ነው። መጽሐፉ በተለይም "የደብረዘይት ደናግል" የተባሉትን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር የነበሩ ደናግልን ሕይወትና ክብር ካስዳሰሰ በኋላ፣ "በሕይወቷ ሁሉ ዓይኖቿን ከፈጣሪዋ ያላነሳች እንደ አዕዋፍ (በመንፈስ) ወደ ሰማያት የከነፈችና የቅዱሳን መላእክት ወዳጅ የሆነች ሴት" በተባለላት በቅድስት ማርያም መግደላዊትና (ገጽ ፺-፺፩) ከሀብታም ቤተሰቦቿ ብዙ ሀብት የወረሰችና ሀብትዋን ሁሉ አምላክዋን ለማገልገል ያዋለችውን፣ የአልዓዛርና የማርያም እኅት የሆነችውን፣ ቅድስት ማርታ የመሠረቷቸውን የደናግል ማኅበሮች ያስነብበናል። በእነዚህ ምዕራፎች ሕይወታቸው የተዳሰሱ ቅዱሳት ደናግል ታሪክ ስናነብ መታለፍ የሌላባቸው ነጥቦች አሉ። በዚህ መጽሐፍ በቀጥታ ገድላቸው ከተዳሰሰላቸው 30 የሚሆኑ አንስት ደናግል ለድንግልና ሕይወት ፈታኝ የሆኑ እንደ ምድራዊ ሀብት (ባዕለ ጸጋነት)፣ ሥልጣን፣ ውበት፣ ወጣትነት፣ ምድራዊ ዕውቀት (ፍልስፍና) ድል አድርገው ያለፉ ናቸው። ከእነዚህ 36% የሆኑት ከባዕለ ጸጋ ቤተሰብ የተገኙ አልያም ባዕለ ጸጋ የሆኑ፣ 43% የሚሆኑት ከባለሥልጣን ቤተሰብ የተገኙና ለሥልጣን የታጩ፣ 33% የሚሆኑት በውበታቸው የታወቁ፣ 32% የሚሆኑት በምድራዊ ዕውቀት የበለጸጉ እንደሆኑ በቀጥታ የተነገረላቸው ናቸው። ይህ ማለት ግን የተቀሩት በቀጥታ የበዓለ ጸጋ ልጅ ነበረች፤ በውበቷ ነገሥታቱ ለጋብቻ አጯት፤ በምድራዊ ዕውቀት ምትክ*

አልነበራትም፣ ወዘተ፣ በሚሉ አልተገለጹም እንጂ አልነበሩም ማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል። ሌሎች በጣም በርካቶች ከጣዖት አምላኪ ቤተሰብና ጣዖት አምላኪ የነበሩ በመሆናቸው የተጋድሎአቸውን ክብር ከፍ ያደርገዋል።

የመጽሐፉ ሁለተኛው ክፍል *ገዳማዊ መብራት ወይም የገነት ዕንቍ* በመባል ስለምትታወቀው የ ፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን *አብሪ ኮከቧ* ጣማፍ ኄራኒ የቅድስና ሕይወት የሚተርክ ነው። ጣማፍ ኄራኒ ቅዱሳን ከሆኑ ቤተሰቦቹዋ፣ በቅድስት ድንግል ማርያምና በሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ፍጹም ምልጃ በ፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ተወለደች። የፋውዜያ እናት ፋውዜያን ለመውለድ በምጥ ስትሠቃይ፣ በቅድስት ድንግል ማርያምና ቅዱስ ጊዮርጊስ ተራዳኢነት በሰላም መገላገልዋንና ቅድስት ድንግል ማርያም ለፋውዜያን (ጣማፍ ኄራኒ) እናት "እርሷ የእኛ እንጂ የአንቺ ልጅ አይደለችም። በመልካም አስተዳደግ አሳድጊያት" እንዳለቻት (ገጽ ፻፳፰ - ፻፳፱) ተጠቅሶአል። ቤተሰቦቹዋ "የእኛ ናት" የሚለውን የእመቤታችንን ቃል በአግባቡ ባለመረዳት፣ ልጃቸው የምትሞትባቸው እየመሰላቸው ዘወትር ይሰጉ ነበር። የወላጆቿ ከቅዱሳን የነበራቸው ሕብረት (በተለይም ቅድስት ድንግል ማርያም፣ ቅዱስ ጊዮርጊስና ሰማዕቱ ቅዱስ መርቆሬዎስ)፣ ቤተ ሰባዊ ልግስና (ምጽዋት)፣ የጸሎት ሕይወት በሕጻኗ ፋውዜያ ያሳደረው አዎንታዊ ጫና ከፍተኛ እንደሆነ የሚያስገነዝበው ይህ ክፍል፣ ከዚህ የተነሳ የወላጆቿ መልካም አርአያነት ጣማፍ ኄራኒን ትሑት፣ ለነዳያንና ለምስኪናን የምታግዝና የምትራራ ለጋስ፣ በጸሎት የምትተጋ፣ ምንኵስናን የምትናፍቅ ከትዕቢት የራቀች እንዳደረጋት የታተተበት ነው።

ከዚህ በተጨማሪ፣ በገዳሙ በመጀመሪያዎቹ የጀማሪነት ዘመኑዋ የደረሱባትን ሁሉ ፈተናዎች አልፋ አንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ለምንኵስና መብቃቷንና የምንኵስና ስሟም ኄራኒ[6] (Erene) መባሉዋን ይተርካል። ከመነኮሰችም በኋላ ፈተናው እንዳልተለያት በተለይም ረድ ሆና ከተመደበችበት መነኵሲትና ከእመምኔቷ የደረሰባት ፈተና ሁሉ በመጽሐፉ ተጠቅሶአል። ነገር ግን አቡ ሰይፈን ለቅድስት ኄራኒና ለእመምኔቷ ተገልጦ ቅድስት ኄራኒ ከገዳሙ እንደማትወጣ እንደነገራቸውም ተብራርቶአል። ይህ ክፍል የቅድስት ኄራኒ እመምኔትነቷ በበርካታ አባቶችና እናቶች በትንቢት የተነገረና ለራሷም በብዙ መንገድ እንደተገለጠላት ያሳያል። በተለይም የትውልደ ኢትዮጵያዊቷ እማሆይ ኤፍሮዚና፣ የአባ ሚናስ አል ባራሙሲ (የኋለኛው አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ)፣ ሦስቱ መቃርሶች በሕልም እንደተገለጡላት፣ ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስና የገዳሙ ታላቅ አባት የነበሩ ሰማዕቱ አቡ ሰይፈን እንደተገለጡላትና ትንቢቶቹና መገለጦቹ ቅድስት ኄራኒ የገዳሙ እመምኔት እንደምትሆን የሚያሳዩ እንደነበሩ ለጸሓፍያኑ እንደነገረቻቸው

[6] በወቅቱ የገዳሙ እመምኔት በነበረችው እማሆይ ኬርያ የተሰጣት ስም ነው።

ያስነብበናል። በጥቅምት ፰ ቀን ፲፱፻፶፰ ዓ. ም. የገዳሙ እመምኔት ከሆነች በኋላ ሙሉ ዳዊት በቀን ሁለት ጊዜ እየደገመች እና ከ ፺፻ ጊዜ በላይ እየሰገደች ገዳሙን ወደ ማስፋትና ማደራጀት ትኩረቷ እንዳደረገች በማንሳት ገና ከጅምሩ የነበራት ትጋት ያስረዳል። እመምኔት ከሆነች በኋላ በአቶችን በአንድ ዓይነትና በተመሳሳይ መንገድ ማደራጀቷ፣ ወጥ የሆነ የአገልግሎት ሥርዐት መዘርጋቷ፣ ቋሚ መንፈሳዊ ጉባኤያት ማስፋፋቷ፣ አዲስ ቤተ መጻሕፍት መክፈቷ፣ የዕደ ጥበብ መሥርያ ሕንፃ ማስገንባቷና ከዚህም የተነሣ የገዳማውያን ዕድገትና ሥርዐት ችቦ አብሪ (ፋና ወጊ) እንደሆነች ይነግረናል። ከዚህ ባለፈም መነኮሳይያቱ በቅዳሴ ጊዜ ስለ እጅ ሥራዎቻቸው ሲነጋገሩ "ምን ዓይነት ጠባይ ነው?" በማለት፣ የተቀበለችው ቅጣትና ከዚህም የተነሳ ከማንም ምንም ዓይነት የቃላት ልውውጥ እንዳትሰማ ጆሮዋን በጥጥ ለመድፈን መወሰን መድረሱዋንና በዚህም እመምኔቷን ጭምር በምልክት ብቻ ለማናገር እስከመቁረጥዋ ራሷ ቅድስት ኄራኒ ትናገራለች።

የመጽሐፉ ሦስተኛ ክፍል ጣማፍ ኄራኒ ከሢመቷ በኋላ የጀመረችውን ገዳሙን የማስፋፋትና የማደራጀት ሥራ አጠናክራ መቀጠሏን የሚተርክ ነው። ይህ ክፍል፣ ቅድስቲቱ የመነኮሳት ቁጥር ከዕለት ወደ ዕለት መጨመሩን በመረዳት፣ ባለ ፫ ፎቅ የነበረውን ሕንፃ ወደ ፬ ፎቅ ማሳደግ፣ የገዳሙ ይዞታ የነበረን መሬት ማስመለስ፣ ከከተማ ወጣ ያሉና ጸጥታ የሰፈነባቸውን አከባቢዎች በመፈለግ መሬት መግዛት፣ ወዘተ. ዋና ትኩረቷ አድርጋ መሥራቷን የሚያሳይ ነው። በዚህም በብዙ ተጋድሎ ባገኘችው ቦታ የመሠረት ድንጋይ በሚቀመጥበት ወቅት፣ መዝሙረ ዳዊትና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፣ የብረት መስቀል፣ የደረቀ ኅብስት (የቡራኬ ዳቦ)፣ የጊዜውንና የቦታውን ታሪክ የሚገልጽ ቅጽ፣ በወቅቱ የቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ የነበሩትን፣ የብፁዕ አቡነ ሲኖዳ ፫ኛን እና የሀገሪቱን ፕሬዚዳንት፣ የሆስኒ ሙባረክን ስም ያለበትን መዝገብ በሳጥን አድርገው ከመሠረት ድንጋዩ ሥር እንዲቀመጥ እንዲሁም ግልባጩ በገዳሙ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ እንዲቀመጥ አድርጋለች። ቅድስቲቱ ገዳማትን ለማስፋት ከነበራት ጽኑ ፍላጎት የተነሣ አንድ መሬት ለማግኘት ለ፴፰ ዓመታት ለፍታለች። ከዚህ በተጨማሪ፣ ክፍሉ ጣማፍ ኄራኒ በሕይወት ዘመኗ ፳፺ ጊዜ ቀዶ ሕክምና ያደረገች ነገር ግን በምንም ዓይነት ለሕመም እጅ የማትሰጥና በውጭ ሀገር (በብዛት በአሜሪካ) አልጋ ላይ ተኝታ በነበረችበት ጊዜ'ኳ የእመምኔትነት ኃላፊነቷን ዘንግታ የማታውቅ ጠንካራ ክርስቲያን እንደነበረች በምሳሌ ያትታል። ጣማፍ ኄራኒ ጥቅምት ፳ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ከዚህ ዓለም ጉዞ አርፋለች[7]። ጣማፍ ኄራኒ ሕይወቷ ሁሉ ቅዱሳንን የመሰለ በመሆኑ "ስለ አንተ ስል ሁሉን ለመቻል የተዘጋጀሁ አድርገኝ፣

[7] ኄራኒ ሰላም፣ ፍቅር ማለት መሆኑን የነሐሴ ፳፩ ስንክሳር ይገልጻል። ይሁንና ነሐሴ ፳፩ የሚነበበው ስንክሳር ስለ ጣማፍ ኄራኒ ሳይሆን በመጀመርያው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ስለነበረች ሌላ ኄራኒ መሆኑ ልብ ይሏል።

ከሕመምህም ጥቂቱን ስጠኝ እያልሁ እጸልይ ነበር" በማለት ራሷን የሰጠችበትና "እኔ ግን በሕመም ዘመኔ ሁሉ እግዚአብሔር እንዲፈውሰኝ ጠይቄው አላውቅም" (ገጽ ፻፻፵፫) ያለችው ለብዙ ክርስቲያኖች በተለይም ለመነኮሳትና መነኮሳይያት አርአያ የሚሆን ነው።

የዚህ መጽሐፍ አራተኛ ክፍል "*በፍቅር የደመቀ ገዳማዊ ሕይወት*"በሚል ርእስ የቀረበ ሆኖ ሦስት ምዕራፎችን ይዟል። ይህ ክፍል ክርስቲያኖች በፍቅር ቢኖሩ እንዴት ፍጹምነት ደረጃ ሊደርሱ እንደሚችሉ ማሳያዎችን በመጥቀስ የሚዳስስ ነው። ለዚህም አባ እንጦንስ ደቀ መዛሙርቱን ሲመክር፣ ወደ ፍጹምነት ለመድረስ የፈለገ መነኰስ በዕውቀት አበባ ያሸበረቀ፣ በጥበብ የበለጸገ፣ ራሱን ዝቅ ያደረገ መሆን እንዳለበት ያነሳል። ይህ በቅዱስ እንጦንስ የተገለጸው ሐሳብ፣ ቅዱስ መቃርዮስ "*ብርሃናዊ ልብስ*" በሚል ይጠራዋል። መጽሐፉ ቅድስት ኄራኒን ለመንፈሳዊ ዕድገት ያደረሳትና ከፍ ከፍ ያደረጋት ይህ ብርሃናዊ ልብስ እንደሆነ ያስረዳል። በዚህ ምዕራፍ ሌላው የተነሳው አንኳር ጉዳይ በገዳሙ በትሕትናቸውና በንጽሕናቸው ለብዙዎች ምሳሌ የሆኑና በተጋድሎአቸው፣ በትሕትናቸው፣ በፍቅራቸው፣ በአገልግሎት ትጋታቸው ወዘተ. የታወቁ ቅዱሳት አንስት ታሪክ ነው።

የዚህ መጽሐፍ አምስተኛውና የመጨረሻው ክፍል "*ጣማፍ ኄራኒ ሐዋርያዊት እናትና መሪ*" በሚል ርእስ በሦስት ምዕራፋት የቀረበ ነው። ይህ ክፍል በጣማፍ ኄራኒ ጸሎት አመካይነት የተፈጸሙ የተለያዩ ተአምራት ተካተውበታል። በተለያዩ ማኅበራዊ ችግሮች ውስጥ ያሉ፣ መውለድ እየፈለጉ መውለድ ላልቻሉ፣ በተለያዩ በሽታዎች የሚሠቃዩ የነበሩ ሁሉ በቅድስት ኄራኒ ጸሎት አማካይነት በተአምር ፈውስና ድኅነት እንዳገኙ የሚያሳዩ ምስክሮች ተካተውበታል። እማሆይ ኄራኒ በገዳሟ በአገልግሎት በነበረችባቸው ጊዜያት ብቻ ሳይሆን በሕመም እየተሠቃየች በነበረችበት ወቅት ጭምር ብዙዎችን በጸሎቷ ፈውስን የምታሰጥ ቅድስት እንደነበረች ያሳያል። ከዚህ በተጨማሪ፣ የጣማፍ ኄራኒ ለገዳማዊ ሥርዐትና መምሪያ ያላት ቀናዒነትና ክብር ተዳሰበታል። ይህን ታላቅ ገዳም ለማስተዳደር እመምኔት ስትሆን ገና የ፴ ዓመት ወጣት የነበረች ብትሆንም የጥንት አበውን ገዳማዊ ሥርዐት ለመጠበቅና ለማስጠበቅ በዘመኑ የነበሩትን የግብጽ ፓትርያርክን፣ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ ትእዛዝን በመንፈሳዊ ጥበብ የተቃወመችበት አጋጣሚ ለብዙዎች ምሳሌ የሚሆን ነበር። ገዳሙ ራሱን መቻል አቅቶት በመንበረ ፓትርያርክ ይደጎም ስለ ነበር ቅዱስነታቸው የገቢ ምንጭ ይሆናል ብለው በማመናቸው በገዳሙ እንዲተገበር ያዘዙት ፕሮጀክት የገዳማውያንን ሕይወት የሚያዛባ ነው ብላ በማመኗ ወደ ቅዱስነታቸው ቀርባ "የተከበሩ መናኒው አባ ሚናስ[8]

[8] ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ ፓትርያሪክ ከመሆናቸው በፊት ይጠሩበት የነበረ ስም ነው።

የቅብጥን የምንኩስና ሕይወት በሚገባ የኖሩ የሚወዱ ሆነው ሳሉ፣ በምን ምክንያት ነው በእርስዎ ዘመነ ጵጵስና እንዲህ ዓይነት የምንኩስናን ሥርዐት የሚጥስና የመነኩሳትን ሕይወት የሚያዛባ ሐሳብ ሊያፈልቁ የቻሉት?" (ገጽ ፫፻፷፮) በማለት ተቃውሞዋን አሰምታለች። ቅዱስነታቸውም አቤቱታዋን ስለተቀበሏት የገዳሙ ክብር እንዲጠበቅ ሆኖአል።

## ፫. የመጽሐፉ ጠንካራና ደካማ ጐን

*ዝክረ ቅዱሳን አንስት ዘተዋሕዶ - ፩* በብዙ ጎኑ በጠንካራነቱ የሚነሣ መጽሐፍ ነው። ድርሰቱ አምስት መጻሕፍትን በአንድ ሽክፎ የያዘ ሲሆን የታሪክ ፍሰቱም ያለመቆራረጥ የቀረበ ነው። ይህም አንባቢ የመጽሐፉን ታሪክ በቀላሉ እንዲረዳው ያደርጋል። ከመጀመርያው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ ፳ኛ መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ የነበረውን የቅዱሳት አንስት ሕይወት፣ አጠቃላይ ገዳማዊ ሥርዐትና ትውፊት ለመረዳት ምቹ አድርጎታል። መጽሐፉ የትርጉም ሥራ እንደመሆኑ ብዙ ሊቃኑ፣ ሊብራሩ፣ ሊተረጎሙ የሚገባቸው መኖራቸው እሙን ነው። ተርጓሚዋ ለእነዚህ ጉዳዮች በግርጌ ማስታወሻ ተጨማሪ ማብራሪያዎችን በመስጠት፣ በመተርጎምና በማቃናት ለአንባቢ እንዳይጎረብጥ ይልቁንም ወጥ ሥራ መስሎ እንዲታይ ያደረገችበት ጥረት በጠንካራነቱ ሊነሣ የሚገባው ሌላ ነጥብ ነው። የመጀመሪያው ክፍል፣ ተርጓሚዋ እንደገለጹት፣ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጎልቶ የሚነገረው የአበው ሕይወት፣ ተጋድሎና ተአምር ነው። ይህ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከአበው ጋር ብቻ የተቆራኘ እንዲመስል አድርጎት ቆይቷል። ይህ መጽሐፍ የቅዱሳት አንስት የሕይወት ታሪክ፣ ተጋድሎና ተአምር በቤተ ክርስቲያን የጎላ ሚና እንዳለው በማሳየት የጎደለዉን ሞልቷል፤ ለመሰል ሥራዎችም በር ከፋች ሆኗል የሚል እምነት አለኝ። ተርጓሚዋ ለቃላት አመራረጥና ለፊደላት ጥራት ያደረገችው ጥንቃቄ እንዲሁም ለዐረፍተ ነገር አወቃቀር ለቃላት መረጣ የሰጠችው ትኩረት ይበል የሚያስብል ነው።

መጽሐፉ ብዙ ጠንካራ ጎኖች እንዳሉት ሁሉ የራሱ የሆኑ ውስንነቶች ተስተውለውበታል። ለምሳሌ ያህል፣ በዚህ መጽሐፍ የቀረበው መቅድም ጸሓፊዎቹ ለመጀመሪያው መጽሐፍ በዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ክፍል የቀረበ መሆኑ ገልጸዋል። ይሁንና ተርጓሚዋ በመኻል (ለዚህ መጽሐፍ እንዲያመች ይመስላል) "በአምስት ክፍል ተከፋፍሎ የቀረበው መጽሐፍ" የሚል ጨምራበታለች (ገጽ ፳፯)። ምንም'ኳን ይህ የራሷ ሐሳብ መሆኑን በግርጌ ማስታወሻ ላይ ብታብራራም ከጸሓፊዎቹ መቅድም ጋር መካተት አልነበረበትም። አስፈላጊ ቢሆን'ኳ ለብቻው በተርጓሚዋ መግቢያ ላይ ማለቅ ነበረበት። ሌላው ክፍተት የቁጥሮች ግድፈት ነው። በመጽሐፉ ክፍል አምስት ምዕራፍ

፩ እና ምዕራፍ ፪ የቀረቡ ቁጥሮች ትክክለኛ ብያኔአቸውን አልያዙም። በዚህ ክፍል ምዕራፍ አንድ "በጣማፍ ኄራኒ ጸሎት አመካይነት የተፈጸሙ ተአምራት" በሚል ሥር የቀረቡ ዝርዝሮች ፩ ብለው መጀመር ሲገባቸው ፲፩ ብለው ይጀምራሉ። ከዚህም የተነሣ የተዘረዘሩት ተአምራት ፲፮ መሆን ሲገባቸው ፳፮ እንደሆኑ ተደርገው ተዘርዝረዋል። በዚሁ ምዕራፍ "ኡምና ኄራኒ ከሀገር ውጭ በነበረችባቸው ጊዜያት በጸሎቷ ኃይል የተፈጸሙ ተአምራት" በሚለው ሥር የተዘረዘሩት አራት ቢሆኑም ከላይኛው የቀጠለ በሚመስል መልኩ ፴ ሆነው ቀርበዋል። በመጨረሻው ምዕራፍ "ጥቂት መነኮሳይያት የሰጡት ምስክርነት" በሚል ሥርም አንድ ብሎ መጀመር ሲገባ ከምዕራፍ አንድ የቀጠለ በሚመስል መልኩ ፴፩ ብሎ በመነሣት በመጽሐፉ የቀረቡ ፳፪ ምስክርነቶች ፶፪ እንደሆኑ አስመስሎታል። እንዲሁም በግርጌ ማስታወሻ ፫ ገጽ ፴፫ "ግርጌ ማስታወሻ ፲፰ ገጽ ፴፰ ላይ ይመልከቱ" ቢልም በገጽ ፴፰ የግርጌ ማስታወሻ ፲፰ የለውም። ይልቁንም ግርጌ ማስታወሻ ፲፯ን ለመጠቆም ይመስላል። መጽሐፉ ክፍል አንድ ገጽ ፴ ሲጀምር ከዚህ በፊት ያሉ የመጽሐፉ ገጾችን የሚገልጹ ምንም ዓይነት ቁጥሮች አልተቀመጡበትም። ከዚህ በተጨማሪ፣ የመጽሐፉ ተርጓሚ መጻሕፍቱን ስትተረጉም የተጠቀመችባቸው ማጣቀሻዎች አልተገለጹም። አቻ ትርጉም ለመፈለግ፣ ቃላት ለማረምና የቃላቱን ትርጉም ለመበየን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶችን ለመተርጎም የትኛውን እትም እንደተጠቀመች ወዘተ፣ ለአንባብያን አልጠቆመችም።

## ፱. ማጠቃለያ

ይህ ዝክረ ቅዱሳት አንስት ዘተዋሕዶ ፩ በሚል የቀረበልን መጽሐፍ በዝርዝር ጭብጦቹ እንደተነሳው በርካታ አበርክቶዎች ያሉት ነው። በዘመናችን የድንግልና ሕይወት እንደ ኋላ ቀርነትና ያለመሠልጠን በሚቆጠርበት ዘመን ኦርቶዶክሳውያን ከዓለማዊነትና ከዘመናዊነት ብይን ራሳቸውን ነጻ አውጥተው በድንግልና እንዲከብሩ የሚነተጉት ነው፡ ፡ ይህን በዚያ ዘመን የነበረውን የደናግል ቅዱሳት አንስትን ሕይወት ስናነብ፣ የእነሱን የግል ሕይወትና የቤተ ክርስቲያን ታሪክን መረዳት ብቻ ሳይሆን ለዘመናዊ የታሪክ ተመራማሪዎች ታላቅ አበርክቶ ያለው መሆኑን እንረዳለን። ምክንያቱም በዘመኑ በየሀገሩ/ከተማ/አህጉር የነበረው የሰዎች የአኗኗር ባህል፣ ነገሥታቱና አስተዳደራቸው፣ ግዛቶችና ገዢዎቻቸው የመሳሰሉ ስለዘመኑ ምንነት ምስክር የሚሆኑ ናቸውና።

መቼም እንደ ዘመናችን ሕገ ቤተ ክርስቲያን የተጣሠበት፣ ሥርዓተ ገዳም የተረሳበትና የፈረሰበት፣ የመነኮሳት አኗኗር ሥርዐትና ቅጥ ያጣበት፣ ድንግልናዊ ሕይወት የተናቀበት ዘመን የለም። የዚህ መጽሐፍ በዚህ ዘመን መታተም ወቅቱ የሚፈልገውና ብዙ ክፍተትን የሚሞላ ነው። በዘመናችን ሴኩላሪዝም (ዓለማዊነት) በፈጠረው ጫና የድንግልና ሕይወት የማይቻል እስኪመስል ድረስ ተሰርቷል። ይህ መጽሐፍ በ ፭ኛው መክዘ የነበሩ ደናግል ቅዱሳት አንስትን ሕይወት በማሳየት የተሳሳተውን አረዳድ የሚቀይር ጉልበት ይዞ መጥቷል። ይልቁንም በዚህ የማይቻል በሚመስልበት ዘመን የማይቻል የሚያስመስሉት ጉዳዮችን በመርታት ለበለጠ ክብር መብቃት እንደሚቻል የሚያሳይ በመሆኑ ወቅቱን የጠበቀ ያደርገዋል።

ለዘመናት የሀገርና የቤተ ክርስቲያን የማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ሆነ የጥበብ ምንጭ የነበሩ የሀገራችን ገዳማት በዘመናችን የበጎ አድራጊዎችን እጅ የሚጠብቁ ሆነዋል። ከዚህ የተነሣ መነኮሳቱ ከገዳማቸው እየተሰደዱ በየከተማው የሚዞሩና ለተለያዩ ፈተናዎች በተለይም ለረጅዎቻቸው ፍላጎት ተገዢ እየሆኑ ይገኛሉ። ሌሎች ደግሞ ራሳቸውን ለመደጎም ሲሉ የተለያዩ የልማት ሥራዎችን በሚሠሩበት ወቅት ከሥርዓተ ገዳሙና ከገዳማዊ ሕይወት ወግና ሥርዐት እያፈነገጡ ለብዙ ትችት እየተዳረጉ ናቸው። ይህ መጽሐፍ፣ ገዳማት በልማትም ሆነ በሰው ኃይል ራሳቸውን ለመቻል በሚያደርጉት ጥረት ኦርቶዶክሳዊ ትውፊትንና ሥርዓተ ገዳምን በጠበቀ መንገድ እንዴት ማከናወን እንደሚችሉ ዓይን ገላጭ ሐሳቦችን የሚለግስ መንፈሳዊ የትርጉም ሥራ ነው።

# ዋቢ ጽሑፎች

አዜብ በርሄ (ውርስ ትርጉም)። (ነሐሴ ፳፻፰)። *ዝክረ ቅዱሳት አንስት ዘተዋሕዶ ፩*። ጃጃው አታሚዎች እና ዴቨሎፐርስ ኃ. የተ. የግ. ማ።

አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ። (፲፱፻፹)። የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ።

መጽሐፈ ስንክሳር ግዕዝና አማርኛ። (፳፻፲፬)። መጋቢት እስከ ጳጕሜን። ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት።

መጽሐፈ ስንክሳር ግዕዝና አማርኛ። (፳፻፲፪)። ከመስከረም እስከ የካቲት። ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት።